# ከኢዴአፓ-መድህን የተሰጠ መግለጫ

## ከወቅቱ የአሜሪካን ምርጫ የበለጠ መማር የሚገባን በራስ መተማመንን ነው!

44ኛው የአሜሪካን ፕሬዚዳንት ምርጫ የዓለምን ትኩረት ተቆጣጥሮ ሰንብቷል። ይህም የሆነው ያለምክንያት አይደለም።ይኸውም በአንድ በኩል ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ አፍሪካዊ ትውልድ ያለው አሜሪካዊ በምርጫው ጠንካራ ተፎካካሪ ሆኖ የቀረበበት ወቅት በመሆኑ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በአሁኑ ወቅት አሜሪካ በአለም ላይ አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅእኖ ለማሳደር ካላት ብቃት አንፃር ምርጫው የአለምን ትኩረት በዚህ መጠን መሳቡ ምክንያታዊ ነው። አገራችን ኢትዮጵያ ከእነዚህ ሁለት ምክንያቶች አንፃር ማለትም አፍሪካዊ የጥቁር አገር በመሆኗና በአለም አካልነቷም (በተለይም በአፍሪካ ቀንድ አገርነቷ) የአሜሪካን ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ ተፅእኖ የሚመለከታት በመሆኑ የወቅቱን የአሜሪካንን ምርጫ ትኩረት ሰጥታ መከታተሏ የማይጠበቅ አይደለም።

የኢዴአፓ- መድህን አባላት እንደማንኛውም ዜጋ ምርጫውን በትኩረት ስንከታተለው የቆየን ቢሆንም ምርጫው በዋናነት የአሜሪካንን ሕዝብ ዕጣ ፈንታ የሚወስን መሆኑን በማመንና የፓርቲ አባሎቻችንም በአሜሪካን የምርጫ እጩዎች ላይ የየራሳቸው የተለያዩ አመለካከት እንደሚኖራቸው በመገመት ከሌሎች ፓርቲዎች በተለየ እንደ ፓርቲ ድርጅታዊ አቋም ወስደን መግለጫ ሳንሰጥበት ቆይተናል። ነገር ግን በአንድ በኩል ሌሎች ፓርቲዎች በጉዳዩ ላይ ድርጅታዊ አቋም ወስደው መግለጫ ሲሰጡበት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በርካታ ኢትዮጵያውያን በባራክ ኦባማ መመረጥ አገራችንም ከፍተኛ የለውጥ አጋጣሚ እንደሚፈጠርላት በማሰብ ከልብ ሲደሰቱ ስናይ በተገቢው መንገድም ይሁን ያለአግባብ ጉዳዩ የአገራችን የፖለቲካ አካል እየሆነ መምጣቱን በመገንዘብ እንደ ኢዴአፓ-መድህን የአሜሪካንን ምርጫ በጥቅሉ በምን መልኩ እንዳየነው ይህንን መግለጫ ለመስጠት ወደናል።

ኢዴአፓ-መድህን በዘንድሮው የአሜሪካን ፕሬዚዳንት ምርጫ አፍሪካዊ አሜሪካዊው ባራክ ኦባማ በምርጫ ዘመቻው ወቅት የአሜካንን ሕዝብ ልብ ለማሸነፍ የሚያስችል የሣብ

የበላይነት አሣይተው የአሜሪካን ሕዝብ ፕሬዘዳንት ለመሆን መብቃታቸው በራሱ ትልቅ ትርጉም ያለው ታሪካዊ ክስተት ነው ብሎ ያምናል፡፡ በአንድ በኩል የዘር መድሎ ሰለባ በመሆናቸው ምክንያት ለዘመናት የመብት ጥያቄ ትግል ውስጥ ለነበሩት ጥቁር ሕዝቦች የባራክ ኦባማ ለዚህ ታላቅ ኃላፊነት መብቃት ለራሳቸውና ለልጆቻቸው ከፍተኛ የሞራል ተሃድሶ የሚያጎናፅፍ ታሪካዊ ድል ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ጥቁር ሕዝቦችን ከሌሎች የተለዩ የተፈጥሮ የአስተሳሰብ አናሳነት እንዳላቸው አድርገው ለሚያስቡ የሕብረተሰብ ክፍሎች ስለ ጥቁር ሕዝቦች የነበራቸውን አስተሳሰብ እንዲመረምሩ የወቅቱ የባራክ ኦባማ ድል ትልቅ ምክንያት የሚሆን ነው፡፡ በተለይም እንደምርጫ ዘመቻው ሁሉ ባራክ ኦባማ በወደፊቱ የአስተዳደር ዘመናቸው ውጤታማ የሚሆኑ ከሆነ የእርሳቸው ለዚህ ድል መብቃት በወደፊቱ የጥቁር ሕዝቦች ስኬታማነት የሚኖረው ድርሻ የበለጠ ታሪካዊ ሆኖ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

የወቅቱ የአሜሪካን ምርጫ ከጥቁር ሕዝቦች ጥቅምና ፍላጎት አንፃር ያለው ታሪካዊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ከዴሞክራሲያዊ ሂደትነቱ አንፃር ምርጫው ለእንደኛ ዓይነቶቹ ታዳጊ አገሮች ብዙ ትምህርት የሚቀሰምበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ይኸውም - አንደኛ የአሜሪካን መንግሥት ወይም የወቅቱ የቡሽ አስተዳደር በተፎካካሪ ፓርቲዎች መካከል ጣልቃ ሳይገባና በምርጫው ሂደት ላይ ከራሱ ጥቅም አንፃር ምንም አይነት ተፅዕኖ ሳይፈጥር ነፃና ገለልተኛ ምርጫ ሲያካሂድ ማየታችን፤ ሁለተኛ በምርጫው ተወዳዳሪ የነበሩት ፓርቲዎችና እጩዎች እርስ በርስ ተከባብረውና በተቻለ መጠን ጨዋ የምርጫ ዘመቻ አካሂደው የሕዝቡን ልብ በያዙት አማራጭ አስተሳሰብ ለማሸነፍ ሲጥሩና በመጨረሻም የምርጫውን ውጤት ያለማቅማማት "እንኳን ደስ አለህ" ተባብለው ሲቀበሉ ማዬታችን፣ ሦስተኛ አብዛኛው ሕዝብ ፍፁም ነፃ በሆነ አእምሮ የቀረቡለትን እጩዎች ከአገሩና ከራሱ ጠቅም አንፃር በመገምገምና በምርጫውም ሁለንተናዊ ተሳትፎ በማድረግ የራሱ ፈቃድ መገለጫ የሆነውን እጩ ሲመርጥ ማዬታችን፤ አራተኛ እንደ ምርጫ ቦርድ የመሰሉትና ሌሎች የአገሪቱ የዴሞክራሲ ተቋማት ከማንኛውም ፓርቲ ተፅእኖ ነፃ በመሆን የአንድ አገርና ሕዝብ የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ዋስትና መሆናቸውን በተግባር በምርጫው ሂደት ላይ ማዬታችን፤ አምስተኛ አብዛኛዎቹ መገናኛ ብዙሃን ከአድሎና ከወገንተኝነት በፀዳ ሁኔታ ምን ያህል በተመራጮችና በመራጩ ሕዝብ መካከል አገናኝ ድልድይ ሆነው ሲያገለግሉና አንዳንድ

ጊዜም ተፎካካሪዎች ከጥላቻ ቅስቀሳ የፀዳ የምርጫ ዘመቻ እንዲያደርጉ የራሳቸውን በጎ ሚና ሲያሳድሩ ማዬታችን ብዙ ትምህርት እንድንቀስም የሚያስችል ነው፡፡

እንደ ኢዴአፓ-መድህን እምነት የወቅቱ የአሜሪካን ምርጫ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው መልኩ ሁላችንም - ማለትም እንደ መንግሥትና እንደ ገዥ ፓርቲ፣ እንደ ተቃዋሚ ፓርቲ፣ እንደ መራጭ ሕዝብ፣ እንደ ዴሞክራሲያዊ ተቋምና እንደ መገናኛ ብዙሃን የየድርሻችንን ልንማርበት የሚገባ እጅግ የሚያስቀና ሂደት ነው፡፡ ኢዴአፓ- መድህን ከዚህ ሂደት ከልቡ ተምሮበታል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የተወሰኑ የኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ባራካ ኦባማ ወይም የዴሞክራቲክ ፓርቲ የአሜሪካንን ምርጫ ስለአሸነፉ ብቻ የኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ ይለወጣል ብለው በእርግጠኝነት በማመን በደስታ ሲፈነድቁ ማየታችን ከማስገረም አልፎ እንዳስደነገጠን በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

በኢዴአፓ-መድህን እምነት እንደ አሜሪካን ያሉ አገሮች በእኛ አገር ጉዳይ ላይ ሊያሳድሩ የሚችሉት ተፅእኖ መኖሩ አጠያያቂ ባይሆንም የኢትዮጵያ ችግር በዋናነት ሊፈታ የሚችለው ግን በእኛው በኢትዮጵያዊያኑ ጥረትና ትግል እንጂ በማንኛውም የውጭ ሃይል ሊሆን አይችልም፣ አይገባምም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ኢትዮጵያዊያን በራስ መተማመን ስሜት የራሳችንን ችግር በራሳችን ለመፍታት የምናደርገውን ሰላማዊ ትግል በሂደት የሚሸረሽርና የአሜካሪንን መንግስት የዲፕሎማሲ ታሪክም በውል ያላገናዘበ ስሜታዊ አስተሳሰብ በመሆኑ በጥንቃቄ ሊጤን የሚገባው ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን ከአሜሪካን የወቅቱ የምርጫ ሂደትም ሆነ ከባራካ ኦባማ ታሪካዊ አሸናፊነት ልንማር የሚገባን በራስ መተማመንንና የመንፈስ ጥንካሬን እንጂ የውጭ ኃይሎች ጥገኛ መሆንን አይደለም፡፡

ሠላምና ሕብረብሔራዊነት ዓላማችን ነው!

ሕዳር 4 ቀን 2001 ዓ.ም
አዲስ አበባ